DISTRICT OF COLUMBIA OFFICE OF UNEMPLOYMENT COMPENSATION
DEPARTMENT OF EMPLOYMENT SERVICES

# የስራ ፍለጋ መስፈርት የመረጃ ወረቀት

ከ ኦገስት 30 2021 ጀምሮ፣ እያንዳንዱ ለስራ አጥነት ጥቅም የሚሞላ ሰው ስራ እየፈለጉ መሆኑን ማረጋገጫ መላክ አለባቸው። ለበለጠ መረጃ እና ለጥቅሙ ለማመልከት dcnetworks.org ይጎብኙ።

በፌደራል እና ዲስትሪክት ህግ መሰረት ከ ኦገስት 30 ጀምሮ የስራ ቅጥር አገልግሎት ዲፓርትመንት (ዲኦኢኤስ) የስራ ፍለጋ ማረጋገጫ መጠየቁን እንደገና ይጀምራል። አመልካቾች የስራ አጥነት ጥቅም ለማግኘት ካመለከቱ በኋላ ፣የሚስማማቸውን ስራ እየፈለጉ መሆኑን ማሳየት ይኖርባቸዋል።ይህ ጥያቄ አሁንም በማመልከት ላይ ለሚገኙ አመልካቾች ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

የስራ ፍለጋው ጥያቄ ቢያንስ በሳምንት ሁለት ስራ መፈለጋቸውን ማሳየት ይኖርባቸዋል።

## የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴ የሚባለው:

- በአካል፣ በደብዳቤ፣ በስልክ፣በፋክስ፣ በድህረ ገፅ ወይም በኢሜል ስራን ማመልከት
- የስራ መፈለጊያ ዝግጅቶች (ጆብ ፌር) ላይ መሳተፍ
- ስራ መስራት እንደሚፈልጉና ስለ ክፍት የስራ ቦታዎች ከቀድሞ የስራባልደረቦች ወይም ተመሳሳይ ስራ ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር መነጋገር
- ቀጣሪዎችን ማነጋገር
- ስራ ፈላጊ ኤጀንሲዎችን ወይም አስቀጣሪ አገልግሎት ሰጪዎችን መጠቀም
- የወርክፎርስ ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ ወይም በዲኦኢኤስ የሚሰጡ ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ

## ሌሎች ማወቅ ያለባችሁ ጠቃሚ መረጃ:

- አመልካቾች የስራ ማመልከቻ ወይም ሬዙሜ ለቀጣሪ ማስገባት አለባቸው፣ ወይም የቀጣሪውን የቅጥር ቅደም ተከተል በመከተል።
- አመልካቾች ለአንድ ስራ በዙ ጊዜ ማመልከት አይፈቀድላቸውም፤ የቀጣሪው የቅጥር ሁኔታ ካልተቀየረ በስተቀር።

ዲኦኢኤስ የአመልካቹን የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴ ለማየት በማንኛውም ጊዜ ማመልከቻው ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ሊጠይቅ ይችላል፤ ስለዚህ ስራ የፈለጋችሁበትን ዝርዝር መረጃ አስቀምጡ። አመልካቾች ለዲኦኢኤስ ስራ የፈለጉበትን መረጃ መላክ የለባቸውም ካልተጠየቁ በስተቀር።

በምትጠየቁበት ጊዜ ስራ የፈለጋችሁበትን መርጃ ካላቀረባችሁ የስራ አጥነት ጥቅማችሁን ልትከለከሉ ወይም ጥቅማችሁ ሊቋረጥ ይችላል። አመልካት በሚጠይውቅበት ጊዜ ሰነዶችን ማቅረብ ካልቻለ ለጥቅሙ ብቁነትን ሊያሳጣ እና ከፋይ ሊያደርጎት ይችላል።

ለበለጠ መረጃ እና ለጥቅሙ ለማመልከት አመልካቾች dcnetworks.org ላይ ማመልከቻ ፖርታሉን ማግኘት ይችላሉ።

በስራ አጥነት ኢንሹራንስ ወይም በአሜሪካን ሬስኪዩ ፕላን ላይ ላሉ ጥቅሞችን ብቁ ለመሆን እነዚህን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል።
የሚከተሉት ፕሮግራሞች የኤአርፒኤ አካል ናቸው (ሴፕቴምበር 4 2021 ያበቃል):

የወረርሽኝ የስራ አጥነት ድጋፍ (ፒዩኤ)

የወረርሽኙ ድንገተኛ ስራ አጥነት ድጋፍ(ፒኢዩሲ)

የፌደራል የወረርሽኙ ስራ አጥነት ድጋፍ (ኤፍፒዩሲ)

የተቀላቀለ ገቢ የሚያስገቡ ስራ አጥነት ድጋፍ (ኤምኢዩሲ)

DOES.DC.GOV